# የፈተና አወጣጥ ፖሊሲን የሚመለከት መመሪያ

## I. መግቢያ

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የተማሪዎችን ውጤት የመገምገም ስራ የባለሞያ ሰራተኞች ኃላፊነት እንደሆነ ያምናል። የፈተና ውጤት በሥርዓተ ትምህርት ከተቀመጡት መስፈርቶች አንፃር የተማሪዎችን የአካዳሚ ብቃት ደረጃ የሚያሳይ መሳሪያ ነው። እነዚህ ደንቦች የፈተና ውጤት እና የግምገማ አሰራርን በመላው የትምህርት አስተዳደር ክልል የማቀናጀት ዓላማ አላቸው። ለተማሪዎች የአካዳሚ አፈፃፀማቸውን በሚመለከት መረጃ በመስጠት የፈተና ውጤት ግልፅ የትምህርት ግቦችን በማዘጋጀት ያገለግላል።

በፖሊሲ IKC መሰረት የሚከተሉት ደንቦች በፈተና አሰጣጥ ሂደት የሚያታየውን የተማሪውን ለውጥ በመገምገም አቅጣጫ በማመልከት እና መረጃ በመስጠት ያገለግላል።

## II. የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ የውጤት አሰጣጥ እና የሪፖርት ካርድ ቅርፃች

የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የመዋእለ-ህጻናት ውጤት ሪፓርት የሚቀናበረው የውጤት አሰጣጥ መስፈርት (የስኮሪንግ ርቢክ) በመጠቀም ነው። ረቢክ በተማሪው በመዋእለ ህጻናት የትምህርት ወቅት አንድ የሚፈልግውን የክህሎት እውቀት ለማወቅ ከታለመው ግብ አንጻር ተማሪው የሚያሳየውን ውጤት ለውጥ ያመለክታል።

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የተሻሻለ በደረጃ ላይ የተመሰረተ የተማሪዎች የውጤት ሪፖርት ከክፍል አንድ እስከ አምስተኛ ድረስ ላሉ ተማሪዎች ይጠቀማል። ዓላማው ልጆች ከክፍል ደረጃ መመዘኛ አንፃር በምን ደረጃ ላይ እንዳሉና በየጊዜው የሚያሳዩትን ለውጥ በማሳየት ለወላጆችና አሳዳጊዎች ትርጉም ያለው መረጃ ማቅረብ ነው። ከቨርጂኒያ የትምህርት ደረጃ መመዘኛ እና የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሥርዓተ ትምህርት ጋር በተቀናጀ መልኩ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የእድገት ሪፓርት ለወላጆችና አሳዳጊዎች በክፍል ደረጃ ስለሚጠበቁ የእውቀት ደረጃዎች፣ ክህሎቶች እና የአፈፃጸም መለኪያዎች በየክፍል ደረጃ የተማሪዎችንና ልጆች እያንዳንዳቸውን እንቅስቃሴ ከሚጠበቅባቸው አንፃር በምን ላይ እንደሚገኙ ዝርዝር መረጃ ይሰጣል።

ከቨርጂኒያ የትምህርት ደረጃ መመዘኛ እና የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሥርዓተ ትምህርት ጋር በተቀናጀ መልኩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የእድገት ሪፓርት ለወላጆችና አሳዳጊዎች በፈደላት የሚገለፅ ውጤት በእያዳንዱ ኮርተር (ሴሚስተር) የተማሪዎችንና ውጤት አፈፃፀም ዝርዝር መረጃ ይሰጣል።

A. በመዋእለ ህጻናት ደረጃ ከሚጠበቀው የተቀመጠ ደረጃ መመዘኛ አንፃር በእያንዳንዱ ተለይቶ በተቀመጠ መስፈርት መሰረት ተማሪው ስለአሳየው ለውጥ የአስተማሪዎች ዝርዝር መግለጫ የያዘ መረጃ በመዋእለ ህጻናት የእድገት ሪፖርት ይካተታል። የአፈፃፀም መጠን አመልካቾች እና የመዋእለ ህፃናት ተማሪዎች ሊያሳዮ የሚገባቸውን ብቃት ደረጃ የሚያሳይ የሚከተሉት ውጤት መስፈርቶች ይጠቀማል፤

> በአካዳሚክ ዙሪያ ነጥብ አሰጠጥ መስፈርት፤
>
> M - በተከታታይ ወጥነት ባለው መልኩ ለርዥም ግዚያት ደረጃውን ያሟላ
>
> P - ደረጃውን ለማሟላት ለውጥ በማሳየት ላይ ያለ
>
> B - ደረጃውን ለሞሟላት ተፈላጊውን ለውጥ ለማሳየት የጀመረ
>
> N -ደረጃው ምን እንደሆነ ያልተረዳ
>
> INA- ከደረጃው ጋር የተዋዋቀ ሆኖም በእርሱ መሰረት ያልተመዘነ

B. በአንደኛ ደረጃ የእድገት ሪፖርት (ክፍል 1-5) አስተማሪዎች በተዘጋጀ መስፈርት ላይ የተመሰረተ የተማሪውን ውጤት አሰጣጥ ብቃት የሚያሳይ የፈተና ውጤት መስጠት አለባቸው። የኮርስ ይዘት ምዘና የሚከተሉትን ያካትታል፤ ህይወት፣ ስራ እና የዜግነት ክህሎቶች፣ የቋንቋ ስነጥበብ፣ የማህበራዊ ጥናቶች፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ ፣ የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት እና ጤና ፣ ስእል ስነጥበብ፣ አጠቃላይ ሙዚቃ እና ባንድ/ስትሪንግ ።

የውጤት ደረጃዎች

4 ሁልግዜም በተከታታይ በኮርተሩ(ሴሚስተሩ) የተማረውን የጠለቀ የእውቀት ግንዛቤ እና ክህሎቶች የብቃት ደረጃ ማሳየት

3 ብዙውን ጊዜ በኮርተሩ(ሴሚስተሩ) የተማረውን የእውቀት ግንዛቤ እና ክህሎቶች የብቃት ደረጃ ማሳየት

2 አንዳንድ ጊዜ በኮርተሩ(ሴሚስተሩ) የተማረውን የእውቀት ግንዛቤ እና ክህሎቶች የብቃት ደረጃ ማሳየት

1 አልፎ አልፎ በኮርተሩ(ሴሚስተሩ) የተማረውን የእውቀት ግንዛቤ እና ክህሎቶች የብቃት ደረጃ ማሳየት

NT በዚህ በኮርተሩ(ሴሚስተሩ) አልተማረም።
NA እንዲተዋወቅ ተደርጎል ነገር ግን በዚህ በኮርተሩ(ሴሚስተሩ) አልተፈተነም።

C. አስተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ (ከክፍል 6-12) ትምህርት ውጤት በፊደላት የሚገለፅ ሪፓርት ይሰጣሉ።

<u>የሁለተኛ ውጤት አሰጣጥ፤ የመጨረሻው ውጤት ስሌት</u>

- ሁሉም የሁለተኛ ደረጃ የመጨረሻ ውጤት የሚሰራው በየተርሙ የተገኘውን ውጤት አማካኝ ጭማቂ ስሌት በመስራት ነው።
  - የሁለተኛ ደረጃ ክሬዲት የማይሰጥበት የሁለተኛ ደረጃ ኮርስ ትምህርት
    - (የ1ኛ ኮርተር ማእከላዊ ጭማቂ ውጤት + 2ኛ ማእከላዊ ጭማቂ + 3ኛ ማእከላዊ ጭማቂ + 4ኛ ማእከላዊ ጭማቂ / 4 ድምር በአራት ማካፈል።)
  - የሁለተኛ ደረጃ ክሬዲት የሚሰጥበት ኮርሶች፤
    - ( የ1ኛ ኮርተር ማእከላዊ ጭማቂ ውጤት + 2ኛ ማእከላዊ+3ኛ ማእከላዊ+ 4ኛ ማእከላዊ ጭማቂ + የመጨረሻ ፈተኛ ማእከላዊ ውጤት / 5 ድምር በአምስት ማካፈል።)

- የኮርተር ማእከላዊ ውጤት F ያገኘ የመጨረሻ ፈተኛ ውጤት በሚሰላበት ወቅት ከ50 በታች መውረድ አይኖርበትም።

## <u>የሁለተኛ ደረጃ  ክሬዲት የማይሰጥበት የሁለተኛ ደረጃ ኮርስ ትምህርት የፈተና አሰጣጥ</u>

| ኮርተር አማካኝ | ፊደል ነጥብ (ግሬድ) |
|---|---|
| 93-100 | A |
| 90-92 | A- |
| 87-89 | B+ |
| 83-86 | B |
| 80-82 | B- |
| 77-79 | C+ |
| 73-76 | C |
| 70-72 | C- |
| 67-69 | D+ |
| 60-66 | D |
| 50-59 | F |
| | I |
| | NR |
| | P |
| | WP |
| | WF |

## <u>የሁለተኛ ደረጃ ክሬዲት የሚያስገኝ ኮርሶች  የፈተና ውጤት ሚዛን፤</u>

| | | ክሬዲት ማግኘት | | | ለሁለተኛ ደረጃ ክሬዲቲ የተጠራቀመ (ክዩምሌቲቭ) GPA ኮሊቲ ነጥብ  እንዲካተት ይደረጋል። ክሬዲት ጂ.ፒ.ኤ.(GPA) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ኮርተር አማካኝ ጭማቂ | የፊደል ነጥብ (ግሬድ) | ክሬዲት ማግኘት | ለሁለተኛ ደረጃ ክሬዲቲ የተጠራቀመ (ክዩምሌቲቭ) GPA ያካትታል። | ኤፒ(AP)/DE/ ኦነር(Honors) ኮሊቲ ነጥብ ማካተት | በከፍተኛ ደረጃ ምደባ (AP) ጥምር ምዝገባ ኮርስ ኮሊቴ ነጥብ | ኦነር ኮርስ ኮሊቲ ነጥብ | መደበኛ (ስታንዳርድ) ኮሊቲ ነጥብ |
| 93-100 | A | አዋ | አዋ | አዋ | 5.0 | 4.5 | 4.0 |
| 90-92 | A- | አዋ | አዋ | አዋ | 4.7 | 4.2 | 3.7 |
| 87-89 | B+ | አዋ | አዋ | አዋ | 4.3 | 3.8 | 3.3 |
| 83-86 | B | አዋ | አዋ | አዋ | 4.0 | 3.5 | 3.0 |
| 80-82 | B- | አዋ | አዋ | አዋ | 3.7 | 3.2 | 2.7 |
| 77-79 | C+ | አዋ | አዋ | አዋ | 3.3 | 2.8 | 2.3 |
| 73-76 | C | አዋ | አዋ | አዋ | 3.0 | 2.5 | 2.0 |
| 70-72 | C- | አዋ | አዋ | አይ | 1.7 | 1.7 | 1.7 |
| 67-69 | D+ | አዋ | አዋ | አይ | 1.3 | 1.3 | 1.3 |
| 60-66 | D | አዋ | አዋ | አይ | 1.0 | 1.0 | 1.0 |
| 50-59 | F | አይ | አዋ | አይ | 0.0 | 0.0 | 0.0 |
| | I | አይ | አይ | አይ | | | |
| | NR | አይ | አይ | አይ | | | |
| | P | አይ | አይ | አይ | | | |
| | WP | አይ | አይ | አይ | | | |
| | WF | አይ | አይ | አይ | | | |

| | | |
|---|---|---|
| I | ያልተሞላ (ኢንኮምሊ.ቲ) | በፖሊሲ IFA መሰረት ለተማሪ የኮርተር አማካኝ ጭማቂ (I) ነጥብ ሊሰጥ ይችላል። በሕክምና ወይም በሌላ አስገዳጅ ምክንያት በአስተዳደር ስምምነት ያለው ምክንያት ካልቀረበ በስተቀር እነዚህም የመጨረሻ ነጥብ ውጤት ስሌት ከመሰራቱ በፊት ወደተገቢው የኮርተር ነጥብ መቀየር ይኖርበታል። |
| NR | አስገዳጅ ተፈላጊ አይደለም (Not Required) | አንድ ተማሪ በአንድ ኮርተር የክፍሉ አማካኝ ጭማቂ ውጤት ላይኖረው ይችላል (በዝውውር እና በሌሎች ምክንያቶች) NR ሊሰጥ ይችላል። እነዚህም  በመጨረሻው የኮርስ አማካኝ ጭማቂ ስሌት ውስጥ የማይካተት እንደባዶ ሊታይ ይችላል። |
| P | አልፎል(Pass) | የክፍል መመዘኛ ውጤት አለፈ/ ወደቀ በሚል መመዘኛ ውጤት የሚሰጥ። ሁለተኛ ድጋፍ መስጫ ክፍሎች/ የማሻሻያ ፕሮግራሞች እና የመንጃ ፈቃድ ሥልጠና ውጤት የሚመዘኑት አለፈ/ ወደቀ በሚል ይገለፃሉ። |
| WF | ከኮርስ ማቆረጥ | ይኸ የሚሰጠው ተማሪው  የF ነጥብ አግኝቶ ክፍሉን ያቆረጠ እንደሆነ ነው። |
| WP | ከኮርስ ማቆረጥ | ይኸ የሚሰጠው ተማሪው  የማለፊያ ነጥብ አግኝቶ ክፍሉን ያቆረጠ እንደሆነ ነው። |

### III. የውጤት መስጫ ጊዜያት

A. ይፋ የውጤት ሪፖርት በዘጠኝ ሳምንታት ላይ የተመሰረተ በአንደኛ ደረጃ ወይም ሁለተኛ ደረጃ ሪፖርት ካርድ

1 አንደኛ ደረጃ በዲያግኖስቲክ እና ፎርማቲቭ ምዘና በተገኘ መረጃና ስሚቲቭ ምዘና ጥምር ላይ የተመሰረተ በወጣው የተግባርና የቤት ስራ ደረጃ መስፈርት መሰረት በመጠቀም ተማሪው በዘጠኝ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ቢያንስ ዘጠኝ ነጥብ ማግኘት ይኖርበታል።

2 ሁለተኛ ደረጃ፤ በዲያግኖስቲክ እና ፎርማቲቭ ምዘና በተገኘ መረጃና ስሚቲቭ ምዘና ጥምር ላይ የተመሰረተ በወጣው የተግባርና የቤት ስራ ደረጃ መስፈርት መሰረት በመጠቀም ተማሪው በዘጠኝ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ቢያንስ ዘጠኝ ነጥብ ማግኘት ይኖርበታል።

3 የግል የትምህርት እቅድ(IEP) ያለው የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች ተማሪዋቹ በእቅዱ ያለውን ግቦች ለማሳካት እና በየኮርተር የሚቀያየሩ ተያያዥነት ያላቸውን አላማዋች ።

4 ለቤት ስራ የሚሰጥ ነጥብ ከሥርዓተ ትምህርት የቅድም ተከተል አፈፃጸም ጋር የሚጣጣም እንዲሁም ከሚጠበቀው የመመዘኛ ደረጃ አንፃር የተማሪውን ለውጥ ማወቅ፣ የተሰጡት ውጤቶች ትርጉም ያላቸው፣ አግባብና አስተማማኝ የሆኑ እና ለተማሪው፣ ለወላጅ እና አሳዳጊ የእድገት ለውጡን የመከታተል ሂደት የሚያሳዮ መሆን አለባቸው።

## IV. የተማሪውን ነጥብ ለመወሰን በርካታ መለኪያዋችን መጠቀም

A. ተማሪዋች በመከታተል ላይ ካሉት ከሥርዓተ ትምህርት መስፈርት ጋር በሚጣጣም መልኩ ኋላፊነት ያለባቸውን የተቀመጠውን መስፈርት ሲያሞሉ የነጥብ ውጤት ያገኛሉ።

B. የነጥብ ውጤት የሚያሳየው  የኮርሱን /ሥርዓተ ትምህርት  አላማዋች በማሞላት ተማሪውን የሚያሳየውን ለውጥ በተለያየ መንገድ የመገምገም እና የትምህርት አቀባባል ልዮነትን ያገናዘበ ለምሳሌ ሆኖም በእነዚህ የማይገደብ ፤ የቴክስት የቤት ስራ፣ (የቃል እና የፅሁፍ፣ ልዮ የቤት ስራዋች፣ ምርምር፣ ፈተና/ድንገተኛ ፈተና ፣ ከክፍል ውጪ የሚሰጥ ስራ ፣ፖርትፍሊዋ፣ ፅሁፍ፣ ቲያትር፣ የአሰራር መመዘኛ ተግባራት፣ ፕሮጀክት እና ተያያዝነት ያለው የተማሪ ስራ ውጤቶች። በተጨማሪም አስተማሪዋች ነጥብ ውጤት ሲሰጡ ትብብርና ተሳትፎን እንደመመዘኛ ነጥብ ሊወስዱ ይችላሉ።

## V. የነጥብ አሰጣጥ ሂደት በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ

A. የነጥብ አሰጣጥ ትክክለኛ ፣ ግልፅ እና የተማሪው የመማር ሂደት በትክክል የሚያንፀባርቅ መሆን አለበት።

B. አስተማሪዋች ነጥብ በሚሰጡበት ሂደት በስሜት የመመራትን  የሚያንፀባርቅ ወይም ወገንታዊነት  የሚያሳይ ሁኔታዋች ማስወገድ አለባቸው።

C. የነጥብ አሰጣጥ የተማሪውን ውጤት በትክክል የሚያሳይ፣ ተማሪው የተሰጠውን ኮርስ ይዘት በሚገባ ያወቀ መሆኑን እንጂ የተማሪውን ባህሪ የሚያንፀባርቅ መሆን የለበትም። አስተማሪዋች የነጥብ አሰጣጥን እንደ የግል ስሜት ወገንታዊነት ማሳያ ፣ ተማሪውን ለመሸለም ወይም ለመቅጣት ማዋል የለባቸውም።

D. የውጤት አሰጣጥ መመዘኛ መስፈርት እና ሂደት የፖሊሲ IFA የሚያንፀባርቅ መሆን አለበት። መመዘኛ እና ግምገማ እና ከእርሱ ጋር የተያያዙ የምዘናው ዓለማን በተመለከተ እና ሚዛናዊ የሆነ ለግምገማ አቀራረብ የሚመለከቱ ደንቦች።

## VI. የነጥብ ውጤት ዝውውር አጠቃቀም

የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች በዝውውር የተገኙ ነጥብ ውጤቶችን ይቀበላል ተማሪው የወሰዳቸው ኮርሶች በአካባቢው እና በስቴት ደንቦች ጋር የሚጣጣሙ እስከሆኑ ድረስ።

## VII. የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ክፍል ደረጃ እና የአማካኝ ነጥብ ስሌት

A. በስፕሪንግ የገለፃ ወቅት እና በሌሎችም የገለፃ ፕሮግራሞች የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ሰራተኞች ለወላጆች/ አሳዳጊዎችና ወደዘጠነኛ ክፍል የሚገቡ ተማሪዎች እና ክሬዲት የሚያስገኝ ኮርሶችን የሚወስዱ የመካከለኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ስለክፍል ደረጃ አሰጣጥና እና የአማካኝ የነጥብ ስሌት እንዴት እንደሚሰላ ገለፃ ያደርጋሉ።

B. የተገኘ ነጥብ የክፍል ደረጃ የሚወስን የትምህርት የመጨረሻ ነጥብ ውጤት ውስጥ ይገባል።

C. ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎችን የትምህርት መመዘኛ ደረጃ ጋር በተጎደኘ የሚካሄድ በራሳቸው ፕሮግራም የሚካተቱ ተማሪዎች በክፍል ደረጃ ውስጥ አያካትትም።

D. በ2016 -2017 የትምህርት ዓመት በዘጠነኛ ክፍል የሚጀምሩ ተማሪዎች በትራንስክሪፕታቸው ላይ ከሚያጠናቅቁት የክፍል ደረጃ አንፃር ጂ.ፒ.ኤ.(GPA) የሙቶዮሽ (ፐርሰንታይል) ነጥብ ውጤት ይሰጣቸዋል።

## VIII. ሥርዓተ ትምህርት እና ኮርስ አወጣጥ ዝርዝር መስፈርት

A. በIFA-R መሰረት፤ የመመዘኛ እና ግምገማ ፖሊሲን ማስፈፀሚያ ደንቦች ፣ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች የሚመሩትን የትምህርት ይዘት የሚያሳይ በትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ወይም ለኮርሱ በሚመዘገቡበት ወቅት የእያንዳንዱን የትምህርት ይዘት እንዲደርሳቸው ይደረጋል። ይህ ዝርዝር የእያንዳንዱን ርእስ የሚኖረውን መመዘኛ ደረጃ መስፈርት፤ የተማሪውን ሃላፊነት እና የኮርሱ ይዘት ቅደም ተከተል ያካትታል።

B. በትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ለሚወስዱት እያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ይፋ የሆነ ስርዓተ ትምህርቱን የሚያሳይ እንዲደርሳቸው ይደረጋል። ይህ ስርዓተ ትምህርት ከIFA-R ፖሊሲ ጋር የሚሄድ መሆን አለበት። የመመዘኛ እና ግምገማ ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ደንቦች እና የኮርስ የሚጠበቁ ሁኔታዎችን ፣ የነጥብ አሰጣጥ (በኮርተር መሰረት) እና የኮርስ አሰጣጥ ቅደምተከተል

## IX. አማካኝ (ዌይትድ) ነጥብ ውጤት

A. የተመረጠ አድቫንስ ፕሌስሜንት/ሆነር ክፍልና የኮሌጅ ደረጃ ጥምር ምዝገባ ኮርስዎች የአማካኝ ነጥብ ውጤት ይሰጣል።

## X. የነጥብ አሰጣጥ እና ተገቢ የሆነ የትምህርት ሪኮርድ መያዝ

A. አስተማሪዎች የእያንዳንዱን ተማሪ ነጥብ እንዴት እንደሰጡ የሚያሳይ ተገቢ የሆነ ሪከርድ መረጃ አለባቸው።

B. የአንደኛ ደረጃ አስተማሪዎች በየጊዜው ይህን ሪከርድ እንዲሻሻል ወቅታዊ ያደርጋሉ። የሁለተኛ ደረጃ አስተማሪዎች በየሁለት ሳምንት ይህ ሪከርድ እንዲሻሻል ወቅታዊ ያደርጋሉ የተገኘውን ውጤት በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በተዘጋጀው የኤሌክትሮኒክስ መገልገያ ያወጣሉ (ለምሳሌ፣ ፖወር ስኩል)።

C. ምንም እንኳን አስተማሪው የተማሪውን ነጥብ ውጤት የሚወስን ቢሆንም ርእሰ መምህሮች ከአስተማሪው ጋር በመካከር ነጥቡ እንዲሻሻል የማድረግ የመጨረሻው ስልጣን አላቸው።

D. ተማሪዎችና ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ተማሪው የሚያሳየውን ለውጥ የመከታተል እና ተያያዥ የሆኑ መረጃዎች በየኮርተሩ እና አመቱን በሙሉ ማግኘት መቻል አለባቸው።

የፀደቀው፤ ዲሴምበር 15፣ 2014
የተሻሻለው፤ ጁን 23፣ 2016

የቃላት መፍቻ፤ IKC የነጥብ አሰጣጥ
IFA ምዘና እና ግምገማ
IFA-R የመመዘኛ እና ግምገማ ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ደንቦች IGBI አዳንቫስ ፕሌስሜንት/እና ጥምር የክፍል ምዝገባ